# በቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ የህግ ማሻሻያ ጥያቄ 2011 ዓ.ም
## ሁለተኛ የንባብ ንግግር
## በተከበሩ ኒኮላስ ኮጺራስ፤ አባል ፓርላማ/ MP
## (THE HON. NICHOLAS KOTSIRAS, MP)

አሁን ይህ የህግ ማሻሻያ ጥያቄ ለሁለተኛ ጊዜ የተነበበ ስለሆነ አልፌዋለሁ።

ቪክቶሪያ በሌላው ክፍለ ሃገር በመድብለ ባህላዊ ጉዳይ አመራር ላይ መቀጠል እንድትችል፤ መንግሥት ለቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ አስፈላጊ የሆኑትን ይፈጽማል። ቃል ይገባል። አሁን ያለውን የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽን በተጠናከረና በበለጠ ጥገኛ ባልሆነ ህጋዊ ባለሥልጣን ለመተካት በ2011 ዓ.ም የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ማሻሻያ ህግ ጥያቄ ለዚህ አፈጻጸም ጠቃሚ ክፍል ይሆናል።

ኮሚሽኑ ለመንግሥት መድብለ ባህላዊ ጉዳይ ቢሮ ዋና የአማካሪ አካል ሲሆን እንዲሁም በቪክቶሪያ ማህበረሰብ እና በቪክቶሪያ መግሥት መካከል እንደ አገናኝ ሆኖ ይሠራል። በቪክቶሪያ የተለያየ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ የዘርና የቋንቋ ብዛት ላላቸው ማህበረሰባት ይህ በቅድሚያና በግንባር ቀደም አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ። ይህ ሀሳብ በህግ ማሻሻያው ውስጥ "መለያየት/diversity" በሚለው ቃል ስር ይገኛል።

### ስለ ህግ ማሻሻያ ጥያቄ አጠቃላይ መግለጫ

መንግሥት ለመድብለ ባህላዊ ጉዳይ ማለት የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽንን ያካተተ ሥራ ድርሻ እንደገና ለማዋቀርና ለማጠናከር ቃል በገባው መሠረት የህግ ማሻሻያ ጥያቄ ይቀርባል። የህግ ማሻሻይ ጥያቄ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ሶስት መንገዶች አሉ:

- አንደኛ፤ የህግ ማሻሻያ ጥያቄ የኮሚሽኑን ነጻነት ይጨምራል ይህም አዲስ ህጋዊ የሆነ አካል በማቋቋም ነው። አዲሱ ህጋዊ አካል የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽን ስምን አይቀይርም፣ ነገር ግን ማህበረሰባችንን በማጠናከሩ ላይ ያተኮረ ይሆናል። የኮሚሽኑን ዓላማዎች በተመለከተ የማህበረሰብ ጉዳዮችን ለሚኒስትሩ በቀጥታ በጥናት፣ ሪፖርትና በምክር አድርጎ በማቅረብ ታዲያ ኮሚሽኑ ያለተጽእኖ ነጻ መሆንን ያጠናክራል። እነዚህ ጉዳዮች በክልላዊ የመማክርት ኮሚቴ ሊታዩ እንደሚችሉ ወይም በተለያየ ዓይነት ማህበረሰባት ውስጥ በሌላ የማህበረሰብ መማክርት አማካኝነት፣ ወይም ተመጣጣኝ በሆነ የመንግሥት አገልግሎት፣ የሰፈራ ድጋፍና አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ሊዛመድ ይችላል።
- ሁለተኛ፤ የህግ ማሻሻያ ጥያቄው በክልላዊ የመማክርት ኮሚቴ አማካኝነት በቪክቶሪያ መንግሥትና በቪክቶሪያ ብዛት ያለው ማህበረሰባት መካከል ጠንካራ ግንኙነትን ይፈጥራል።
- ሶስት፤ ለመድብለ ባህላዊ ለየት ባለ አንቀጽ ህግ መሰረት ጠቅላላ የመንግሥት አቀራረብ እንዲሆን የህግ ማሻሻያ ጥያቄ ያስታውቃል።

በተጨማሪም በቪክቶሪያ የመድብለ ባህላዊ ማሻሻያ ህግ ጥያቄ 2011 ዓ.ም ቀደም ሲል የነበረን *የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ አንቀጽ ህግን 2004 ዓ.ም/Multicultural Victoria Act 2004* በሚከተሉት ይተካል:

- የመድብለ ባህላዊ መሰረታዊ መመሪያዎችን ማደስ;
- የአዲስ ኮሚሽንን ዓላማና ሥራ ማበረታታት፣ እንዲሁም
- በመድብለ ባህላዊ በተዛመደ አስፈላጊ ሪፖርት ማቅረብን መቀጠል ይሆናል።

### የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽን

በበለጠ ተጽእኖ የሌለበት የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽን መመስረቱ በመንግሥትና የቪክቶሪያ የተለያዩ ማህበረሰባት መካከል ጠንከር ያለ ግንኙነትን ይፈጥራል።

አዲሱ ኮሚሽን ለቪክቶሪያውያን እርዳታ በመስጠት ላይ ያተኮረ ሲሆን ታዲያ ታማኝና ግልጽ የሆነ ምክር ለመንግሥት እንደሚሰጥ እገምታለሁ።

የኮሚሽን ከተጽእኖ ነጻ መሆን የሚገኘው በአዲሱ ህግና የአስተዳደር ቅንጅት አማካኝነት ሲሆን ይህም እንደ ሃላፊነት ያለው ሚኒስተር፣ በተለያየ ማህበረሰባት ባሉ ጉዳዮችና እድሎች ላይ በቀጥታ ምክር እንዲሰጥ ያስችለዋል።

አዲሱ ኮሚሽን ለእኔ ተጨማሪ የጥናት ሥራዎች፣ የምክር ልገሳና ሪፖርት እንዳለው ሃላፊነት ያለበት ሚኒስተር እንደመሆኑ መጠን ያቀርባል። እነዚህ ተግባራት በኮሚሽኑ ወይም በእኔ ጥያቄ አነሳሽነት ሊሆኑ ይችላል።

የኮሚሽኑን ተግባራት በሪፖርት ለማቅረብ ለኮሚሽኑ ጥናት የሚረዳ መረጃ ለማቅረብ የተጠየቁ የመምሪያ ሃላፊዎች አስፈላጊ የሆነ ጥረት ስለማድረጋቸው ማረጋገጥ አለባቸው።

ለአዲሱ ኮሚሽን የሚሆኑ አስራ ሁለት ኮሚሽነሮች በምክር ቤት ገዥው ሲመረጡ በዚህ ላይ የሚካተ:

- የሙሉ ቀን ሊቀመንበር፣
- የፈረቃ ጊዜ ምክትል ሊቀምንበር;
- ለየት ያለ ችሎታና ልምድ ያላቸው ስምንት የትርፍ ጊዜ ኮሚሽነሮች;
- የፈረቃ ጊዜ የወጣት ተወካይ፣ እና
- በእኔ የተወሰነ የማህበረሰብ ድርጅት የፈረቃ ጊዜ ተወካይ።

አዲሱ ኮሚሽን ከመንግሥት መምሪያዎችና ከኮሚሽን ሊቀመንበር ተጽእኖ ነጻ ሲሆን ታዲያ ሰራተኛ ለመቅጠርና ኮንትራት ለማካሄድ ስልጣን አለው። ሰራተኛ የሚቀጠረው እንደ የህዝብ አገልጋይ ስለሆነ ታዲያ በቪክቶሪያ ህዝባዊ የህግ ስነ-ምግባር መሰረት ነው።

## ክልላዊ የመማክርት ኮሚቴዎች

ለአስተዳደር ግዛት የሚሆን ስምንት የክልላዊ መማክርት ኮሚቴዎች እንዲመሰረት በህግ ማሻሻያ ጥያቄ ይቀርባል። እነዚህ ኮሚቴዎች ከአካባቢ የተለያየ ማህበረሰባት ጋር በቅርበት እንደሚሰራና ታዲያ ለኮሚሽን ተግባራት ስለሚጠቅሙ ጉዳዮች ማለት የክልላዊ ሰፈራና አገልግሎት አቅርቦት መረጃን ለማስተላለፍ ይጠቅማሉ።

ስምንት የትርፍ ጊዜ ኮሚሽነሮች እያንዳንዳቸው የክልላዊ መማክርት ኮሚቴን በመምራት፣ በክልላዊ መንግሥት የተለያየ ማህበራት ለሚያጋጥማቸው ጉዳዮች ማለት ስለመንግሥት አገልግሎትና የሰፈራ ድጋፍን ያካተተ በራሳቸው እውቀትና ችሎታ በመመራት ለችግሮች መፍትሄ ያቀርባሉ።
በህግ ማሻሻያ ጥያቄው ውስጥ ላልተጠቀሰ የክልላዊ መማክርት ኮሚቴዎች ብዛት ያለው ተግባራትን ሲያካትት ይህም:

- አንደኛ፤ በአካባቢው ማህበረሰብ አባላት እውቀትና ችሎታ መሰረት፤ በመንግሥት አገልግሎትና የሰፈራ ድጋፍ አቅርቦትና እንቅስቃሴ ያተኮረ በክልላዊ የተለያየ ህዝብ በኩል ሊሚነሳ ጉዳይና እድሎች መሰረት በማድረግ የክልላዊ መማክርት ኮሚቴዎች ለኮሚሽኑ ምክር ያቀርባሉ።
- ሁለተኛ፤ በቪክቶሪያ ብቅብቅ ለሚሉ የሥራ መስኮች አዲስ ለመጡ ማይግራንትስ እንዲያውቁ ለመርዳት ኮሚቴዎች ከአካባቢ ንግድ አውታሮች፣ ቀጣሪዎችና የአስተዳደር ግዛት ንግድ ልማት ባለስልጣኖች ጋር በመሆን ይሠራሉ።
- ሶስተኛ፤ ኮሚቴዎች ጠቃሚ የሆኑ የክልላዊ ስብሰባዎች ያቀርባል፤ እንዲሁም ለቪክቶሪያ የሚጠቅም ለመምረጥ የተለያዩ ባህሎችና ሃይማኖቶች እንዲከበር እድሎች በማቅረብ ለማህበራዊ ውሕደትና መጣጣም ያበረታታል።

## ለመንግሥት መምሪያዎች የሪፖርት አስፈላጊነት

በህግ ማሻሻያ ጥያቄ መሰረት፤ እንደ ሃላፊ ሚኒስተር መሆኔ መጠን እንዴት መምሪያው እንደተሻሻለ ወይም የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ማህበረሰብ ድጋፍ እንዳገኘ በእያንዳንዱ የፋይናንስ ዓመት የመንግሥት መምሪያዎች ለእኔ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ይህ ቀደም ብሎ በነበረው *የቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ አንቀጽ ህግ 2004 ዓ.ም/Multicultural Victoria Act 2004* የነበረ ግዴታ ነው።

**የመድብለ ባህላዊነት መሰረታዊ መመሪያዎች**

**መንግሥት ጠንካራና አንድነት ያለው ሕብረተሰብ ለማነጽ የአውስትራሊያ ዜግነት መነሻ ሲሆን፤ ታዲያ ግለሰቦች እርስ በርስ እንደሚማሩና አብሮ በጋር በበለጠ ውሕደት ያለውና የተጣጣመ ሕብረተሰብ ለማነጽ ይረዳል። በህግ ማሻሻያ ጥያቄው ላይ የዜግነት ጽንሰ ሀሳብ ለመደበኛ የአውስትራሊያ ዜግነት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፤ ነገር ግን በመድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ላሉ ሰዎች በሞላ ስለሚኖራቸው መብቶችና ሃላፊነቶች ይጠቅሳል። የዜግነት ሀሳብ በሃገራችን ላለ የተለያየ ሕብረተሰብ በጋራ ሃላፊነትን ወስደው በአንድነት ሲያጠናክር፣ እንዲሁም የቀረበው ሀሳብ በዲሚክራቲክ ተቋማት፣ ህጎች፣ ልምድና ‘አግባብ አካሄድን’ ያሟላል።**

**ለአውስትራሊያና ለማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም ቪክቶሪያ ለተለያየ ሁኔታ ባለሀብት እንደመሆኗ መጠን ታዲያ በመድብለ ባህላዊ መሰረታዊ መመሪያዎች ላይ የዜግነት፣ ልምድና የጋራ ሃላፊነት መመሪያን እንዲያካትት የህግ ማሻሻያ ጥያቄው ሀሳብ ያቀርባል። እንዲሁም ፓርላመንት የዜግነትንና መለያየት**/diversity **በመድብለ ባህላዊነት ጽንሰ ሀሳብ ስለመደገፉ፣ የህግ ማሻሻያ ጥያቄው ያቀርባል። በዚህ ላይ የሚካተት መከባበርን፣ መረዳዳትን፣ የመለያየትን**/diversity **እና ቅርስን ማጠናከርና አቅም ላላቸው እንዲሳተፉ እድሉን መክፈት ይሆናል። ሕብረተሰቡ ብዙ ያካተተና ተስማሚ እንደሆነ ለማስመሰል የመድብለ ባህላዊ መሰረታዊ መመሪያ ይረዳል።**

**ማጠቃለያ**

**በቪክቶሪያ የመንግሥት አገልግሎቶች እያደገ ላለው መድብለ ባህላዊ ሕብረተሰባችን ፍላጎት ስለማሟላቱ ለማረጋገጥ የቪክቶሪያ አዲሱ መድብለ ባህላዊ የህግ ማሻሻያ ጥያቄ** 2011 **ዓ.ም**/ Multicultural Victoria Bill 2011 **ስለሚረዳ ታዲያ ብዛት ያለው የማህበረሰባችን ድምጽ በበለጠ ተደማጭነት አለው።**

**በመድብለ ባህላዊነትና ዜግነት ስለሚኖር የቪክቶሪያን አመለካከት የህግ ማሻሻያ ጥያቄው ያጠናክራል፣ እንዲሁም ጠንካራና አንድነት ያለው ሕብረተሰብ ለማነጽ መሰረታዊ ሁኔታን ያቀርባል።**

**የህግ ማሻሻያ ጥያቄው ወደ ምክር ቤት እንዲቀርብ አደንቃለሁ።**